# የቤተ አማራ ስውር ማንነትና በአማራ ስም የተደራጁ ድርጅቶች ሊወስዱት የሚገባ ጥንቃቄ! — ሠዓሊ አምሳሉ ገ/ኪዳን አርጋው

November 2, 2017 05:03

ትናንትና ረቡዕ 22, 2, 2010ዓ.ም. የአማራ ድምፅ ራዲዮ (ነጋሪተወግ) የቤተ አማራ መሥራችና ሊቀመንበር የተባለውን አቶ መሳፍንት ባዘዘው ዳምጤን ጋብዞ አቅርቦት ነበር፡፡ በጣም ይገርማል! እኔ ይሄንን ልጅ ወያኔ በደምብ አድርጎ ያሠለጠነው ካድሬ ይመስለኝ ነበረ፡፡ ለካ እንዲህ ዓይነት ሊሰሙን የሚቀፍና የሚያሸማቅቅ ገንገበት ኖሯል እንዴ ለካ? ለነገሩ እንዲህ ዓይነት ሰው ባይሆን ነበር የሚገርመው፡፡ እንዲህ ዓይነት ንቃተ ሕሊናው ያልበሰለ ደነዝ ባይሆን፣ የዘቀጠ ሰብእና ባይኖረው ኖሮ ወያኔ መጠቀሚያው ሊያደርገው ባልቻለም ነበር፡፡ ኧረ ግን ስንት ነቃ ነቃ ያለና ጮሌ የሚመስል ካድሬ (ወስዋሽ) ሞልቷት የለም እንዴ ወያኔ?

በጣም ነው የገረመኝ፡፡ መናገር የሚፈልገውን ነገር ተቀባይነት ባለው ላቅ ያለ መርሕና ምሁራዊ ተዋስኦ በተንጸባረቀበት መልኩ በርዕዮተዓለም ደረጃ ማስረዳት ቀርቶ ይሄ ሐሳቡን በአግባቡና በቅጡ መግለጽ ማስረዳት የማይችል፣ የሚጠየቀውን ጥያቄ እንኳ መረዳት የማይችል ገንገበት ነው የአማራን ሕዝብ እወክላለሁ ብሎ "የፖለቲካ ድርጅት መሥርቸ በሊቀመንበርነት እየመራሁ ነኝ!" የሚለው? ወይ ሞታችን! ወይ ውርደታችን! ምነው ወያኔ ምነው? ምነው? ነቃ ባለ ሰው እንኳ ልታታይ ብትሞክሪ ምን ነበረበት? ንቀት መሆኑ ነው?

ምን አለ መሰላቹህ አቶ መሳፍንት አማራ ራዲዮ ላይ ቀርቦ "አማራን አንድነት የሚያስመታው ከሆነ፣ የኦሮሞ የራስ መንግሥት ለመመሥረት እንደ እንቅፋት ተቆጥሮ የሚያስመታው ከሆነ፣ ለትግሬውም የራስ መንግሥት ለመመሥረት እንደ እንቅፋት ተቆጥሮ የሚያስመታው ከሆነ፣ ለሸአቢያ ለኤርትራ የራስ መንግሥት ለመመሥረት እንደ እንቅፋት ተቆጥሮ የሚያስመታው ከሆነ አማራስ ከማን ያንሳል?" ብሎ ቁጭ አላ፡፡ ጨመረና "የተለየ ከዚህ በፊት ያልነበረ አስተሳሰብ ይዛ መቅረቧ ነው የቤተ አማራ ጠንካራ ጎኗ!" ብሎ እርፍ አቶ መሳፍንት፡፡ በሱ መለኪያ ሀገርን ማፍረስ ወይም መገንጠል ከማንም አለማነስ ነው፣ ከዚህ በፊት ያልነበረ አስተሳሰብ ማራመድ ጠንካራነት ነው፡፡ ወይ ጉድ ይሄ ነው እንግዲህ መሪያቹህና አስተሳሰባቹህ ቤተ አማራ ነን ባዮች???

"አንዱን አየ ሁሉን አየ!" አሉ እንግዲህ የተሻለ ተብሎ መሪ የሆነው ሰው ይሄ ከሆነ ጭፍሮቹ ተከታዮቹ ደግሞ እንዴት ከዚህ የባሱ ይሆኑ? ነው ያሰኘኝ፡፡ ጥሩ ነው ግን እኔ ደስ ብሎኛል የአማራ ድምፅ ይሄንን ልጅ ይዞ በማቅረቡ በጣም ደስ ብሎኛል፡፡ አለዛማ አሁን ያወቅነውን የልጁን ገንገበትነት እንዴት ለማወቅ እንችል ነበረ? ቤተ አማራ እንደስሙ ውስጡ ያማረ መስሎት ለመቀላቀል የፈለገ የተማረ ዜጋ ካለም ይሄንን መስማቱ ቤተ አማራ ነን የሚሉትን ቡድን ማንነት በደንብ በመረዳት እርሙን ለማውጣት ስለሚያስችለው ይሄ ቃለመጠይቅ መቅረቡ በጣም ጥሩ ነው፡፡

ሶሻል ሚዲያው ላይ ቤተ አማራ ቤተ አማራ ለሚሉት ግን ምን ያህል በመሸማቀቅ እንዳፈርኩላቸው በቃላት ለመግለጽ ይቸግረኛል፡፡ እኔ እኮ ዓላማቸው ምንም ይሁን ምን እነ መሳፍንት በድረ ገጾች ላይ ጽሑፎችን (አርቲክሎችን) በመጻፍ የርዕዮተዓለምና የሐሳብ ፍጭት የማያደርጉት ለምንድን ነው? እል ነበረ፡፡ ለካ ምድረ ገንገበት ከቶውንም የማያውቁት ሆነው ነው ድረ ገጾች ላይ ምሁራዊ ተዋስኦ የሚታይባቸውን ጽሑፎችን የማይጽፉ የነበረው፡፡ የሚያራምደው አቋም ከወያኔ ጋር አንድ ከመሆኑ በተጨማሪ የመሳፍንት ብቃትና አቅም እንዲህ የወረደ ሆኖ እያለ የፖለቲካ (የእምነተ አሥተዳደር) ድርጅት መሥርቶ ለመንቀሳቀስ መሞከሩ ከዚህ ሰው ጀርባ ሌላ አካል መኖሩን ከመቸውም ጊዜ በላይ ግልጽ አድርጎታል፡፡ ዓላማው ምንም ይሁን በእንዲህ ዓይነት ሰው ደካማ አቅምና የማሰብ ችሎታ ድርጅታዊ እንቅስቃሴ ታስቦ ይፈጠራል ብላቹህ ካሰባቹህ የዋህን ናቹህ፡፡

ደሞ ምን ገረመኝ "ጎንደር በኮሎኔል ደመቀ የተቀሰቀሰውን የአማራ ማንነት እንቅስቃሴንና የሕዝባዊ እንቢተኝነት ተቃውሞ የኛ አስተውጽኦ፣ የኛ የትግል ውጤት ነው!" ብሎ እርፍ፡፡ እኛም አላልን ከስንት ዓመታት በፊት ጀምረን ስንት ዋጋ እየከፈልን አማራን ለመቀስቀስ ለማንቃት፣ ታጥቆ ተደራጅቶ አማራነቱን እንዲጠብቅ፣ ከዘር ማጥፋት ጥቃት እንዲከላከል ስንት ነገር በየመጽሔቱ፣ በየማኅበራዊ የብዙኃን መገናኛው ስንት ስንቀጠቅጥ ስንት ስናደርግ የኖርነው፡፡

ለመሆኑ የወልቃይት የአማራ ማንነት እንቅስቃሴ ሲጋጋል ቤተ አማራ የሚባል ነገር እራሱ ከነአካቴውስ መቸ ነበረና? ከተቋቋመ ገና ሦስት ዓመት እንኳን መቸ ሞላውና ነው እንዲህ የሚባለው? እሽ እንደተመሠረተ በአንዳች ተአምራዊ ኃይል ሕዝባዊ ተቀባይነት አገኘና የጎንደርን ዐመፅ ቀሰቀሰ እንበል ግን ታዲያ በሕዝባዊ ዐመፁ ወቅት የጎንደር ሕዝብ "የኦሮሞ ደም ደማችን ነው! በዘር በሃይማኖት የሚከፋፍለንን አንፈልግም!…" ብሎ ኢትዮጵያዊ አንድነቱን አስተጋባ እንጅ የቤተ አማራን ከኢትዮጵያ የመገንጠልን ጥያቄ ነው እንዴ ሕዝቡ ያስተጋባው? እንዴት ሆኖ ነው ታዲያ የቤተ አማራ ውጤት የሚሆነው? እንዴት ነው የሚቃዣው ባካቹህ? የአማራ ሕዝብ የገጠሩን ጨምሮ "ቤተ አማራ የሚባሉት እንዲህ እንዲህ የሚሉ ናቸው!" ሲባል ገና እንዴት እንዴት እንደሚያደርገው ባየሽና ልክሽን ባወቅሽ ምንኛ ደስ ባለኝ ነበረ ምድረ ቅጥረኛ ደናቁርት ሁላ እንኳንና የሕዝብ ተቀባይነት ኖሮሽ ዓላማሽን አንግቦ ሊንቀሳቀስልሽ ይቅርና፡፡

ወይ ሶሻል ሚዲያ! ይሄ ማኅበራዊ የብዙኃን መገናኛ (ሶሻል ሚዲያ) እኮ ሁሉንም እኩል አስቀመጠውና እንዴት አደፋፈረን ባካቹህ! የሶሻል ሚዲያ (የማኅበራዊ የብዙኃን መገናኛ) ነጻ መድረክነት አንዱ ጉዳቱ እንግዲህ ይሄ ነው፡፡ ማኅበራዊ የብዙኃን መገናኛ ለሁሉም ነጻ መድረክ ስለሆነ ማንም ገንገበት ደንቆሮ እየወጣ ቢጤዎቹን ሰብስቦ ዝም ብሎ ቢጮህ በጩኸቱ ውስጥ ፍሬ ነገር ባይኖርም እንኳ ጩኸቱ ስለሚረብሽ ብቻ ትኩረት ማግኘቱ አይቀርም፡፡ እና እነዚህ ምድረ ገንገበት ደናቁርትማ ታዲያ የሚያወሩትን የደነቆረ አስተሳሰብ ቢያራምዱ ምን ይገርማል?

ከላይ እንደገለጽኩት የአማራ ድምፅ ልጁን ጋብዞ በማቅረቡ ሰው እንዲያውቅ ያደረገው ነገር አለና ደስ ብሎኛል፡፡ ነገር ግን ቃለመጠይቁ ቤተ አማራ ለአማራ ሕዝብ አለኝ የሚለውን ተቋማዊ ተዋስኦ በሚፈትሽ መልኩ ቃለ መጠይቁ በሞጋች ጥያቄዎች ታጅቦ መቅረብ ነበረበት፡፡ ቃለ ምልልሱን አዘጋጅቶ ያቀረበው አቶ ተስፋዬ ተክለ ሃይማኖት የፈለገው አቶ መሳፍንት ቤተ አማራን እንዲያስተዋውቅ ብቻ ነው መሰል ቁጥብነት አሳይቷል ሊከራከረውም አልፈለገም፡፡ ነገር ግን አቀራረቡ በጠንካራ ጥያቄዎች ታጅቦ አለመቅረቡ ቃለምልልሱን ደረጃውን ያልጠበቀና ሊያዳምጡት ፍላጎት የማይቀሰቅስ እንዲሆን አድርጎታል፡፡

እኔ ስለ መሳፍንት ያለኝ መረጃ የሚለው መሳፍንት የ12 ክፍል ትምህርት አጠናቆ የተቀመጠ እንደሆነ፡፡ ባይመረቅም የዩኒቨርስቲ ተማሪ እንደነበረ የሚያወራው ወሬ ሐሰት መሆኑን፡፡ አሜሪካ ሊገባ የቻለውም ከሴት ጓደኛው ጋር ቅርብ በሆነ ዓመት ሱዳን ሔዶ ከሱዳን ተነሥቶ መሆኑን፡፡ ልብ በሉ የፖለቲካ ስደተኛ ሆኖ አይደለም፡፡ ልጁ አሜሪካ እስኪገባ ድረስ ምንም ዓይነት የተቃውሞ እንቅስቃሴ አልነበረውም፡፡ ይሄ በሆነበት ሁኔታ ለታዋቂ ተቃዋሚ ኢትዮጵያውያን ፖለቲከኞች (እምነተ አሥተዳደራውያን) እንኳ በሱዳን በኩል የሦስተኛ ሀገር ጥገኝነትን ማግኘት ካከተመለት ዐሥርት ዓመታት ያለፉ በሆነበት ሁኔታ መሳፍንት ጥገኝነት ጠያቂ ፖለቲከኛ መሆኑን የሚያረጋግጥለት መረጃ ሳይኖረው እንዴት በቅርብ ዓመታት ከሴት ጓደኛው ጋር ሱዳን ሔዶ ከሱዳንም የሴት ጓደኛውንም ጭምር ይዞ አሜሪካ የመግባት ዕድል ሊያገኝ እንደቻለ መመርመር ያለበትና አጠራጣሪ ጉዳይ መኖሩን የሚጠቁም ነው፡፡

ይሄ ቡድን ተልዕኮ የተሰጠው ከወያኔ ብቻ አይመስለኝም፡፡ ለኢትዮጵያ ጥፋት ከሚመኙላት ፕሮቴስታንት አሜሪካኖች ጭምርም ይመስለኛል ተልዕኮ የተሰጠው፡፡ ለነገሩ አሜሪካኖቹ ከወያኔ ጋር ሆነው ለኛ ጥፋትና መከራ ተግተው እየሠሩ ያሉት ወያኔ ገና በረሀ እያለ ጀምሮ ተባብረው

ተመሳጥረው ይሠሩ ስለነበረ አንድ ናቸው፡፡ ስለሆነም የእነ መሳፍንት ቤተ አማራ ፕሮጀክት (የሥራ አቅድ) የወያኔና የአሜሪካውያን የጋራ የሥራ አቅድ ሊሆን ይችላል፡፡ ለዚህም ይመስለኛል መሳፍንት በአጭር ጊዜ ውስጥ ያውም የሴት ጓደኛውን ይዞ ጉዳዩ በቶሎ ተፈጽሞለት አሜሪካ ሊገባ የቻለው፡፡

መሳፍንት ከመናፍቃን ቤተሰብ የወጣ ልጅ በመሆኑ እዚህ ኢትዮጵያ እያለም መናፍቅ ነበረ፡፡ ይሁንና ከመናፍቃን ቤተሰብ የወጣ ቢሆንም እሱ ግን አጥባቂ መናፍቅ አልነበረም፡፡ እንዲያውም የተለያዩ ሱሶች ያሉበት እንደሆነ ነው ያለኝ መረጃ የሚያሳየው፡፡ መሳፍንት ቤተ አማራ ውስጥ በኃላፊነት ሰብስቦ የያዛቸው ልጆችም በሙሉ መናፍቃን ናቸው፡፡ ይሄ የአጋጣሚ ይመስላቹሀል? አንድ ወይም ሁለት ፕሮቴስታንት ያልሆኑ በአጋጣሚ የገቡ ይኖሩ ይሆናል የተቀሩት ግን መናፍቃን ናቸው፡፡ መናፍቃን ከጥንት ጀምሮ በዚህች ሀገርና ሕዝቧ ላይ ምን ዓይነት የጥፋት ዓላማና ግብ ይዘው ምን ዓይነት ጥረት ሲያደርጉ እንደቆዩና ምን ኪሳራ እንዳደረሱ ከሀገሪቱ ታሪክ የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ አሁን በዚህ ዘመን ያሉ መናፍቃንም የባዕዳን አባቶቻቸው የቅኝ ገዥ ሰላዮች ልጆች ናቸውና እነዚህ አባቶቻቸው በቀደዱላቸው ፈር በመጓዝ ለሁሉም የዚህች ሀገር የማንነት እሴቶች ጠላት በመሆንና ለማጥፋት በመጣር ምን ዓይነት ቋሚ ጉዳት እያደረሱና ለጠላቶቻችን የፖለቲካ ድል እያስመዘገቡ እንዳሉ በግልጽ የሚታወቅ ጉዳይ ነው፡፡ እናም ይሄ የነ መሳፍንት ማንነታቸውና የተሰጣቸው የቅጥረኝነት ተልዕኮ ነው እንግዲህ እነ መሳፍንትን ከአማራ ሕዝብ ማንነት፣ ታሪክ፣ የወል አስተሳሰብ፣ ታሪካዊ አደራ፣ ባሕል፣ ሃይማኖት፣ ትውፊት፣ ሥልጣኔ፣ የሞራል (የቅስም) ከፍታ ወዘተረፈ. ፍጹም ተቃራኒ በሆነ መንገድ እንዲያስቡና እንዲራመዱ ያደረጋቸውና የጠላቶቻችንን ዓላማ ለማስፈጸም እንዲታትሩ ያደረጋቸው ነው ነጥቡ፡፡

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ሞረሽ ወገኔን ጨምሮ በአማራ ሕዝብ ስም የተደራጁ አንዳንድ ድርጅቶች ከዚህ የጠላቶቻችን ቅጥረኛ ቡድን ጋር ለመሥራት እየተንቀሳቀሱ እንደሆነ ይስተዋላል፡፡ ይሄ ለአማራ ሕዝብ አስከፊና አስደንጋጭ መርዶ ነው፡፡ እነ ሞረሽ ወገኔ የብአዴን ወይም የወያኔ ካድሬዎች ሶሻል ሚዲያው ላይ የቤተ አማራን ጭምብል አጥልቀው ውር ውር ሲሉ ሲያዩ ጊዜ ቤተ አማራ በርካታ የአማራ ወጣቶች ድጋፍ ያለው መሰላቸው መሰለኝ ይሄንን ኃይል ማቀፍ ወይም መያዝ እንደሚገባ አመኑና እነ መሳፍንንትን ማቀራረብ አብሮ ለመሥራት መጣር ጀመሩ፡፡ ቤተ አማራ እንኳንና ደጋፊና የሕዝብ ተቀባይነት የሌለው ሆኖ ቢኖረው እንኳ ይሄ ቅጥረኛ የጥፋት ቡድን ምን ያህል የወያኔንና የባዕዳን ጠላቶቻችንን መርዘኛ የጥፋት ዓላማ ተሸካሚ መሆኑ በግልጽ እየታወቀ ይሄን የጥፋት ቡድን ልክ ለአማራ ሕዝብ ጠቃሚ፣ አሳቢ፣ ተቆርቋሪ አድርጎ በመቁጠር ከዚህ የተመረዘ የጥፋት ቡድን ጋር ለመሥራት ማሰብ እንዴት አዋጭና ጠቃሚ መስሎ እንደታያቸው ፈጽሞ ሊገባኝ አልቻለም፡፡

በተለይ ደግሞ ይሄ ይጥፋት ቡድን ከማኅበራዊ የብዙኃን መገናኛውም (ከሶሻል ሚዲያውም) እንኳ እየከሰመ ወሬው እየጠፋ ባለበት ሰዓት ይሄ መደረጉ በግሌ እጅግ አሳዝኖኛል አስከፍቶቻልም፡፡ ፈጽሞ ብስለትና አስተውሎት የተለየው እጅግ ኃላፊነት የጎደለው እርምጃ ነው እየተወሰደ ያለው፡፡ ይሄንን ቡድን በማግለል፣ የደነቆረና አጥፌ የቅጥረኛ አስተሳሰቡና የጠላት ቅጥረኛነቱ በሕዝብ ዘንድ እንዲታወቅ በማድረግ መቸም ተቀባይነት እንዳይኖረው፣ ተረስቶ እንዲቀርና በራሱ ጊዜ እንዲከስም መሥራት ሲገባ እንደገና አፈር ልሶ እንዲነሣ መርዳት እንዴት ሆኖ ትክክለኛ እርምጃ ሆኖ ሊታያቸው እንደቻለ ፈጽሞ ሊገባኝ አልቻለም፡፡ የምትሰሙኝ ከሆነ ሞረሽም ሆነ ሌሎች በአማራ ስም ተደራጅታቹህ እየሠራቹህ ያላቹህ ወገኖች ከዚህ እጅግ የተሳሳተ እርምጃ ትታቀቡ ዘንድ አጥብቄ ማሳሰብ እወዳለሁ!!!

ለዚህ ጽሑፍ መልስ ለመስጠትም ሆነ "በያዝነውና በምናራምደው አቋም አናፍርም! ለአማራ ሕዝብ እንደሚጠቅም እናምናለን፣ አፋችንን ሞልተን ሸንጣችንን ገትረን መከራከር እንችላለን ና ተከራከረን!" በማለት ከቤተ አማራ በተለይም መሥራች ሊቀመንበር ተብየው መሳፍንት በሬዲዮ (በነጋሪተወግ) ከኔ ጋር ለመከራከር የሚፈልግ ከሆነ ግብዣውን በደስታ የምቀበል መሆኔን ከወዲሁ

ማሳወቅ እወዳለሁ፡፡ ነገር ግን እነ መሳፍንት ማንነታቸውን ያውቃሉና እንኳን በራሳቸው ፍላጎት ተለምነው፣ እንኳን ተለምነው ተገደውም ከኔ ጋር ለመከራከር በፍጹም የሚቀርቡ አይመስለኝም፡፡ መቅረብ ካልፈለጉ ደግሞ እምቢ ከማለታቸው ወይም መቅረብ መከራከር ካለመፈለጋቸው ከአስመሳይ የወያኔ ካድሬዎች ውጭ መስሏቹህ ቤተ አማራን የተቀላቀላቹህ ወገኖቸ ካላቹህ በዚሁ አጋጣሚ የነመሳፍንትን ማንነት የምትረዱ ይሆናል፡፡

ድል ለአማራ ሕዝብ!!! ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!! ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!!!

ሠዓሊ አምሳሉ ገ/ኪዳን አርጋው
amsalugkidan@gmail.com